የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 እና 14

1. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ የተመሰለው የወይን ስፍራ ባለቤት ከበለስ ፍሬ ፍለጋ ስንት ዓመት ተመላለሰ?
ሀ)ሁለት ዓመት ለ)ሦስት ዓመት ሐ)አራት ዓመት መ)አምስት ዓመት

2. የወይን አትክልት ሠራተኛው በለሱን እንዲቆርጣት ሲታዘዝ ምን አደረገ?
ሀ)ቆረጣት
ለ)አፈር እንዲያስታቅፋት እና ፍግ እንዲሚያፈስባት ቃል ገባ
ሐ)የዘንድሮን ዓመት እንዲተዋት ለመነ
መ)ለ እና ሐ

3. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ ከሰይጣን እስራት የተፈታችው ሴት ስንት ዓመት ጎብጣ ነበር?
ሀ)12 ዓመት ለ)28 ዓመት ሐ)18 ዓመት
መ)33 ዓመት

4. ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ማዳን እንደሚገባ በምን መስሎ አስተማረ?
ሀ)በሰንበት በሬ እና አህዮቻቸውን ገለባ ሊያበሉ እንደሚፈቱት ሁሉ ከአጋንንት እስራት በሰንበት መፈታት ይገባል
ለ)ቀበሮ ወደ ጉድጓድ እንደሚገባ ሁሉ የሰው ልጅ በሰንበት መዳን እንደሚችል
ሐ)የወይኑ ባለቤት በለሲቱን እንደተዋት ሁሉ በሰንበት ምንም መስራት እንደማይገባ አስተማረ
መ)ሁሉም

5. "ያችን ቀበሮ" ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ስለማን ነው?
ሀ)ንጉሥ ሰሎሞን ለ)ንጉሥ ሄሮድስ
ሐ)ጲላጦስ መ)ሐናና ቀያፋ

6. በሉቃስ ወንጌል ላይ የበለስ እርሻ ባለቤት, የእርሻ ጠባቂ እና በለስ ሆነው የተመሰሉት እነማን ናቸው?
ሀ) ጌታ, ቅ.ሚካኤል, ሕዝበእስራኤል
ለ) እግዚአብሔር, ቅ.ገብርኤል, የዘመነ ሀዲስ ሰዎች
ሐ) እግዚአብሔር, ጠባቂ መልአክ, የዘመነ ሀዲስ ሰዎች

መ)ሁሉም

7. በበዓል ጊዜ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንን እንድንጠራ አስተማረን?
ሀ)ባለጸጎችን
ለ)ዘመዶቻችንን
ሐ) ጦም አዳሪዎችን
መ) ጎረቤቶቻችንን

8. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 15 ላይ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባቀረበው ምሳሌ ላይ ወደ ምሳው የተጠሩት ሰዎች ካቀረቧቸው ምክንያቶች ውስጥ ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ)ሚስት አግብቻለሁ
ለ)የወይን ስፍራ ገዝቻለሁ
ሐ)እርሻ ገዝቻለሁ
መ)አምስት ጥማድ በሬዎች ገዝቻለሁ

9. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምኩራብ ሲያድን የተቆጣው ማን ነው?
ሀ)የምኩራብ ሹሙ ለ)ሕዝቡ ሐ)የዳነችው

ሴት መ)ሁሉም

10. ከፈሪሳውያን ወገን መጥተው "ሄሮድስ ሊገልህ ይሻልና ከዚህ ሂድ" አሉት ስለ ሰዎቹ ትክክል የሆነው የቱ ነው?
ሀ) ጌታን የሚወዱት ሰዎች ነበሩ
ለ)ለክርስቶስ አዝነውለት ነበር
ሐ)ተአምራት እንዳያደርግ ወንጌል እንዳትሰፋ ብለው ነበር
መ)ሀ እና ለ
11. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ ፍሬ የሌላት በለስ ታሪክ ምን ያስተምረናል?
ሀ) ጸሎትን መላልሶ መጸለይ እንጂ መተው እንዳይገባ
ለ) አልሳካ ያለንን ነገር ሁሉ ቶሎ መተው እንዳለብን
ሐ) ምንም ነገር ላይ ከሦስት አመት በላይ መጸለይ እንደማይገባ
መ) ለ እና ሐ

12. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ላይ ፍሬ የሌላት በለስ ታሪክ ላይ ሦስት አመት መመላለሱ የምን ምሳሌ ነው?

ሀ) የብሉይ፣ ሐዲስ እና የሲያል
ለ) የዘመነ መሳፍንት፣ ዘመነ ነገሥት፣ ዘመነ ካህናት
ሐ) የአዳም፣ የሙሴ እና የዳዊት
መ) የነቢያት፣ የመነኮሳት፣ የጻድቃን

13. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 ጌታ የፈወሳት እንዴት ነበር?
ሀ) "ከደዌሽ ተፈትተሻል" ብሎ
ለ) እጁን በላይዋ ጭኖ
ሐ) በአርምሞ
መ) ሀ እና ለ

14. ሰናፍጭ በመንግሥተ ሰማያት የተመሰለችበት ምክንያት ያልሆነው?
ሀ) ሰናፍጭ የሰማይ ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ እንድትሆን፣ ወንጌልም ሕዝብም አሕዛብም ተሰብስበው ለ) መጥተው እስኪያምኑባት ድረስ ደግ ሕግ ትሆናለች።
ሐ) ሰናፍጭ አንድ ጊዜ የዘሯት እንደሆነ ባመት ባመት ዝሩኝ አትልም፤ ተያይዞ ስትበቅል ትኖራለች፤ ወንጌልም አንድ ጊዜ ተዘርታ ማለትም በመቶ ሃያው ቤተሰብ

ተጀምራ እስከ ምጽአት ድረስ ስትነገር ትኖራለች።
መ) ሰናፍጭ ትንሽ እንደመሆኗ መንግሥተ ሰማያትም ትንሽ ናትና
ሠ) ሁሉም
ረ) ሀ እና ለ

15. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 13 መንግሥተ ሰማያት ከተመሰለችባቸው ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው?
ሀ) ሰናፍጭ
ለ) ፍሬ በሌላት በለስ
ሐ) ሴት ወስዳ ሦስት መስፈሪያ ዱቄትን የለወሰችበትን እርሾ
መ) ሀ እና ሐ

16. ጌታ ራሱን ከመሰለባቸው ምሳሌዎች መካከል ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) ዶሮ ለ) የወይኑ ቦታ ባለቤት ሐ) ኢየሩሳሌም መ) ሀ እና ለ

17. "በበዓል ምሳ ወይም ራት በምታደርግበት ጊዜ ወዳጆችህንና ወንድሞችህን፣ ዘመዶችህንና

ጎረቤቶችህን፣ ባለጸጎች ባልንጀሮችህንም አትጥራ ... "
ሉቃስ 14፡ 12 ላይ ያለው ቃል የሚናገረው ...
ሀ) በምታስተምርበት ጊዜ የተማሩትን አስተምራለሁ አትበል ማለት ነው
ለ) ያልተማሩትን፣ የሚያስተምሩህ የሌላቸውን አስተምር
ሐ) በምትመንንበት ጊዜ የተማሩትን ብቻ ይዤ እመንናለሁ አትበል
መ) ሁሉም

18. "ለነቢይ በኢየሩሳሌም እንጂ ከኢየሩሳሌም ውጪ ተሰቅሎ መሞት አይገባውም" የተባለበት ምክንያት ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ) በምድር መሀከል መድኀኒትን አደረገ ያለው ትንቢት እንዲፈጸም
ለ)የአዳም ራስ እዚያ አለና እሱን ለማዳን እንደመጣ ለማጠየቅ
ሐ)አዳምን ያሳተው አርቄ ራስ በዚያ ወድቆ ነበርና እሱን ለማጥፋት
መ) መልሱ የለም

19. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ላይ ለምሳ የተጠሩት ሰዎች በቀሩ ጊዜ ጌታው አገልጋዩን ማንን እንዲጋብዝ ላከው?

ሀ) ባለስልጣኖችን ለ) ጦም አዳሪዎችን ሐ) ዕውሮችና አንካሶችን መ) ለ እና ሐ

20. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ላይ ጨው የተባለ ምንድን ነው?

ሀ) ጥሬ ጨው ለ) ምናኔ ሐ) ንግሥና መ) ክብር